# የኦሞ ኩራዝ ቁጥር 2 ስኳር ፋብሪካ ማምረት ጀመረ



ከሙከራ ምርት በኋላ ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት ለረዥም ወራት ስኳር ማምረት አቁሞ የነበረው የኦሞ ኩራዝ ቁጥር 2 ስኳር ፋብሪካ ከትላንት ታህሳስ 22 ቀን 2010ዓ.ም ጀምሮ ስኳር በማምረት መደበኛ ሥራውን ጀመረ፡፡

ስኳር ከማምረቱ ከሁለት ቀናት በፊት አገዳ በመፍጨት ሥራ የጀመረው ይህ ፋብሪካ ከሰኔ አጋማሽ 2009 ዓ.ም ጀምሮ ስኳር እንዲያመርት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በዝናብ ምክንያት ላለፉት ስድስት ወራት ወደ ሥራ ሳይገባ ቆይቷል፡፡ የአየር ንብረት መዛባትን ተከትሎ ባለፈው ዓመት በአካባቢው ባልተለመደ ሁኔታ በጣለው ከፍተኛ ዝናብ ሳቢያ በወቅቱ ለፋብሪካው ግብዓት የሚውል ሸንኮራ አገዳ ከማሳ በማውጣት ወደ ፋብሪካ መውሰድ አዳጋች ነበር፡፡

ኮምፕላንት በተባለ የቻይና ኩባንያ የተገነባው ይህ ፋብሪካ በቀን 12 ሺህ ቶን አገዳ የመፍጨት አቅም ያለው ግዙፍ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ሙሉ የማምረት አቅሙ ላይ ሲደርስ በዓመት እስከ 2.5 ሚሊዮን ኩንታል ስኳርና 28 ሚሊዮን ሊትር የሚጠጋ ኤታኖል እንደሚያመርት ይጠበቃል፡፡

ለፋብሪካው ግንባታ ብቻ ከቻይና ልማት ባንክ በተገኘ 6.67 ቢሊዮን ብር ብድር ሐምሌ 2007 ዓ.ም ሥራው በይፋ የተጀመረው የኦሞ ኩራዝ ቁጥር 2 ስኳር ፋብሪካ ባጋስ ከተባለ የስኳር ተረፈ

ምርት ከሚያመነጨው 60 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ውስጥ 20ውን ለራሱ ተጠቅሞ 40 ሜጋ ዋቱን ወደ ብሔራዊ ቋት የመላክ አቅም አለው፡፡

በኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት እየተገነቡ ከሚገኙ አራት የስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ የኩራዝ ቁጥር 2 ስኳር ፋብሪካ አንዱ ሲሆን፣ መጋቢት 14/2009 ዓ.ም የሙከራ ምርት መጀመሩ ይታወሳል፡፡

የኦሞ ኩራዝ ቁጥር 2 ስኳር ፋብሪካ አሁን በምርት ላይ የሚገኙትን ስኳር ፋብሪካዎች (ወንጂ ሸዋ፣ መተሐራ፣ ፊንጫአ፣ ከሰምና ተንዳሆ) ቁጥር ወደ ስድስት አድርሶታል፡፡ በተጨማሪ የአርጆ ዲዴሳ ስኳር ፋብሪካ ከጥር ወር መጨረሻ ጀምሮ ወደ ሥራ እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡

